የኮ/መ/ቁ 286331

ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ልደታ ምድብ 4ኛ ንግድ ችሎት

ዳኛ:- መካ ነስሩ

ከሳሽ:- ኃይብሪድ ዲዛይንስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አሊ መሐመድ ቀረቡ

ተከሳሽ:- ሰረገላ ራይድ ታክሲ ሰርቪስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ሲሳይ ኃይሉ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የንግድ ምልክት ጥሰትን የተመለከተ ሲሆን የከሳሽ ጠበቃ በነሀሴ 29 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከሳሽ በንግድ ሕጉ መሰረት የተቋቋመና ህጋዊ ህልውና ያለው የንግድ ማህበር ነው፡፡ ከሳሽ በንግድ ምዝገባ ቁጥሩ BL/AA/0011785/2008 የሶፍት ዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ ሥራዎች የንግድ ፈቃድ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አውጥቶ፣ በየዓመቱ የንግድ ፈቃዱን በማሳደስ፣ በህጋዊ የሶፍት ዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ የንግድ ሥራ ተሰማርቶ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ ከሳሽ ከሚመለከተው መንግስት አካል የተሰጠውን የሶፍት ዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ ፈቃድ መሰረት ታክሲዎችና ሌሎች የትራንስፖርት አገልግሎት ለመሥጠት ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች፣ የታክሲና የንግድ መኪና ኪራይ አገልግሎት ከሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር በSMS መልዕክት እንዲገናኙና የትራንስፖርት አገልግሎቱን በቴክኖሎጅ ታግዘው በማንኛውም ቦታ ሆነው፣ ቀልጣፋና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ ለደንበኞቻቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የሚያስችል የሶፍት ዌር ቴክኖሎጅ በማልማት ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ ከሳሽ በሕግ አግባብ ከተቋቋመ ጀምሮ" ራይድ RIDE" የሚለው ንግድ ምልክትና የንግድ ሥም በሕግ አግባብ አስመዝግቦና አልምቶ ሥራ ላይ ያዋለው ቴክኖሎጅ መለያ አድርጎ

ከ16,000 በላይ የሚሆኑ ታክሲዎችና የንግድ መኪና ኪራይ ከነሹፌሩ የማከራየት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመሥጠት ህጋዊ ፈቃድ ካላቸው የኮድ03 መኪና ባለሀብቶችን የከተማው የትራንስፖርት ተጠቃሚ ከሆኑ ግለሰቦች፣ አገር በቀል ለሆኑና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በቴክኖሎጅ በማገናኘት ፈጣንና ቀልጣፋ የታክሲና የንግድ መኪና ኪራይ ከነሹፌሩ የመከራየት አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረገ ይገኛል። በሌላ በኩል ከሳሽ ያለማውን ቴክኖሎጅ ተጠቅመው የታክሲና የንግድ መኪና ኪራይ ከነሹፌሩ የማከራየት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፍላጎት ያላቸውን የታክሲና የኮድ 03 መኪና ባለሀብቶች ለዚሁ ሥራ ባደራጃቸው ቢሮዎች እየመዘገበና ህጋዊና ቴክኒካል መሥፈርቶች ካሟሉት ጋር ውል በመዋዋል በየዕለቱ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ያደርጋል።

ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር ተመሳሳይነት ያለው በህጋዊ የሶፍት ዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ የንግድ ሥራ ተሰማርቶ የሚገኝ ድርጅት ነው። ተከሳሽ አገልግሎት የሚሰጡና የትራንስፖርት አገልግሎት ከሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች በቴክኖሎጅ እንዲገናኙ ማድረግ የሚያስችል የሶፍት ዌር ቴክኖሎጅ በማልማት ጥቅም ላይ እንዳዋለ የሚገልጽ ድርጅት ነው። ከሳሽ ቴክኖሎጅ ባለማው አገልግሎት የሚሰጠው፣ከሳሽ በአዋጅ ቁጥር501/1998 መሰረት በ2007 ዓ.ም አስመዝግቦ ባለቤት የሆነበት ሶስት የአማረኛ ፊደሎች ከላይ አራት የእንግሊዘኛ ፊደሎች ከታች ያሉት በጥቁርና ነጭ ቀለም ተጻፈ" ራይድRIDE" የሚለው ንግድ ምልክትና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ያስመዘገበውን "ራይድ RIDE" የሚለውን የንግድ ሥም፣የአገልግሎቱ መለያ አድርጎ በመጠቀም ራይድRAID" ሚለውን ብራንዱን በሰፊው በማሳወቅና በማስለመድ ነው። ሆኖም ተከሳሹ ያለከሳሽ ፈቃድ ከሳሽ የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም የሆነውን RIDE" የሚለውን ቃልና ምልክት የተከሳሹ ሥም ቅጥያ አድርጎ ተከሳሽ የድርጅት ሥም አድርጎ በመጠቀምና(ሰረገላ ራይድ RIDE") የሚል ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሀንና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በማስተዋወቅና መልዕክት በማስተላለፍ፣ ሕጋዊ ጥበቃ የተደረገለትን የከሳሽን የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም የባለቤትነት መብት በማያቋርጥ ሁኔታ በመጣስ ላይ ይገኛል። ተከሳሽ (ሰረገላ Seregela) ከሚለው የድርጅት ሥሙ ቀጥሎ "ራይድ RIDE" በሚለውን የከሳሽን የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም በመጻፍና በመጠቀምና (ሰረገላ ራይድ Seregela ride) ብሎ በመገናኛ ብዙሀን በህትመት፣ በድምጽና በምስል ባስተላለፋቸው ማስታወቂያዎችና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በለቀቃቸው ማስታወቂያዎች እና ባስተላለፋቸው መልዕክቶች በአዋጅ ቁጥር501/1998 አንቀጽ26 ንዑስ አንቀጽ2(ሀ)እና በአዋጅ

ቁጥር980/2008 አንቀጽ17 ንዑስ አንቀጽ1 መሰረት ሕጋዊ ጥበቃ የተደረገለትን የከሳሽን የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም የባለቤትነት መብት በመጣስ በከሳሽ የዕለት ተዕለት ሥራ ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግር እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ተከሳሽ የከሳሽን የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም የባለቤትነት መብት በመጣስ የሚፈጽመው ሆነ ብሎ ከሳሽ ከአምስት ዓመታት በላይ ሰርቶና ብዙ ወጭ አውጥቶ ለህብረተሰቡ ያስለመደውን የንግድ ምልክትና የንግድ ስም እንደዚሁም ከሳሽ በዘርፉ ግንባር ቀደም ሆኖ አገልግሎት በመጀመር ያዳበረውን መልካም ሥምና ዝናና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አመልካች ደንበኞች በማሳሳት፣የእሱን አገልግሎት እንዲጠቀሙ በማድረግ ተገቢ ያልሆነ ጥቅምና ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ነው፡፡ በዚህ በኩል በርካታ የከሳሽ ደንበኞች ተከሳሽ የከሳሽ ቅርንጫፍ እንደሆነ አድርገው በማመን ተከሳሹ ያለማውን ቴክኖሎጅ እንዲጠቀሙ እያደረጋቸው መሆኑን፣ ተከሳሹ ቴክኖሎጅ ታግዘው ስለሰጣቸው አገልግሎት የሚሰማቸውን ቅሬታ ለከሳሽ በሥልክና በአጭር መልዕክት አስተያየት ከሰጡን በኋላ ተከሳሹ ራሱን የቻለና ከከሳሽ የንግድ ድርጅት የተለየ መሆኑን ስንገልጽላቸው፣ የተከሳሽ ሥምና ንግድ ምልክትነት የሚጠቀመው ከከሳሽ ጋር ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ የከሳሽ ድርጅት ነው ብለው እንዳመኑና እንደተሳሳቱ እየገለጹልን ይገኛል፡፡

ተከሳሽ የተለያዩ ሰዎችን መልምሎ የተከሳሽ ደንበኞች የሆኑ የታክሲና የኮድ 03 መኪና ባለሀብቶች ወደ ሥራ እስኪሰማሩ ድረስ በሚቆሙበት ቦታ በመላክ፣ የከሳሽ ደንበኞች ከሳሽ ያለማውን ቴክኖሎጅ ለመጠቀም የተዋዋሉትን ውል በማፍረስ ከተከሳሽ ጋር ቢሰሩ ተከሳሽ የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንደሚሰጣቸውና ተከሳሽ የሚያስከፍለው ኮሚሽን ከከሳሽ ያነሰና ዝቅተኛ ነው የሚል ቅስቀሳ እንዲቀሰቅሱና በማድረግ በከሳሽና በተከሳሽ ደንበኞች ግንኙነት ላይ ባልተገባ ሁኔታ ጣልቃ በመግባት ከፍተኛ የሆነ ችግር እየፈጠረና የሁከት ተግባር እየፈጸመ ይገኛል፡፡ ተከሳሽ (ሰረገላ ራይድ Seregela ride” በሚል መንገድ በሚሰራቸው ማስታወቂያዎችና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በማስተዋወቅና መልዕክት በማስተላለፍ በፈጸመው የመብት ጥሰትና አሳሳች የሁከት ተግባር በከሳሽ ላይ ከብር 100,000 (መቶ ሺ ብር) በላይ የሆነ ጉዳት አድርሷል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ (ሰረገላ) ከሚለው ሥም ቀጥሎ ራይድ ride ” የሚለውን ከሳሽን ንግድ ምልክትና የንግድ ሥም፣ያለከሳሽ ፈቃድ በመጠቀም ሰረገላ ራይድ (seregela ride”) የሚል ሕገ ወጥና አሳሳች ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሀንና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ማስተላለፉን ሙሉ በሙሉ እንዲያቆም፣ ተከሳሽ የከሳሽን ንግድ ምልክትና የንግድ ሥም አውጥቶ የራሱን የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም ብቻ በመጠቀም፣

ሕጋዊ ጥበቃ የተደረገለትን የከሳሽን የንግድ ምልክትና የንግድ ሥም የባለቤትነት መብት እንዲያከብር በአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ26 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ1 መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥልኝ ፤ተከሳሽ የሶሻል ሚዲያ ፕላት ፎርም (ድረገጽ)ተጠቅሞ በከሳሽ ሥራ እየፈጠረ ያለው የሁከት ተግባር እና ተከሳሽ ሰዎችን የከሳሽ ደንበኞች የሆኑ የታክሲና የኮድ 03 መኪና ባለሀብቶች ወደ ሥራ እስኪሰማሩ ድረስ በሚቆሙበት ቦታ በማሰማራት እየፈጸመ ያለው ሕገ ወጥ የሁከት ተግባር ሙሉ በሙሉ እንዲያቆምና ተከሳሽ እየፈጠረ ያለው ሁከት እንዲወገድ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1149 መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥልኝ፤ ተከሳሽ በፈጸማቸው ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ህገ ወጥ የመብት ጥሰትና የሁከት ተግባራት በከሳሽ ላይ ለደረሰው ኪሳራ ብር 100,000 (መቶ ሺህ ብር) ተከሳሹ ካሳ እንዲከፍል እንዲሁም በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪ እና ኪሳራ ተከሳሽ እንዲተካልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰነድ እና ምስክሮች ስም ዝርዝር አያይዘው አቅርበዋል፡፡

ተከሳሽም የከሳሽ ክስ ደርሷቸው ጥቅምት 10 ቀን 2013 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ብይን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 18 እና 19 ላይ የወል የንግድ ምልክት ፈቃድና ምዝገባ የሚሰጠው ለሰራተኛ ማህበራት ወይም ፌዴራሽኖች የሰራተኞቻቸውን መብት ለማስጠበቅ ብቻ ሲሆን ይሄውም የወል የንግድ ምልክቱ ከሚተዳደርበት መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ ጋር ለፅ/ቤቱ በቀረበ ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ራይድ(Ride) የተሰኘው የንግድ ምልክት ከሰራተኛ ማህበራት ወይም ፌድሬሽኖች ጋር የተያያዘ ሳይሆን የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍን የሚመለከት ጥቅል የሆነ የወል(generic) ስም ነው፡፡ የእንግሊዘኛ ዲክሽነሪ ትርጉሙም "Ride means a journey made on a horse, bicycle,or motor cycle,or in a vehicle."ይላል፡፡ ይህም ሙሉ የትራንስፖርት ዘርፉን ጠቅልሎ የያዘ ወይም የሚገልፅ የወል ስም(generic name) መሆኑን ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የወል መጠሪያ በሆነ ስም ደግሞ የንግድ ምልክትም ሆነ የንግድ ስም ፈቃድና ምዝገባ ማውጣት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም መንግስት በብቸኝነት (በmonopoly) ከተቆጣጠራቸው እንደ ኢትዮ ቴሌኮምና አየር መንገድ ከመሳሰሉት የአገልግሎት ዘርፎች ውጪ ያሉት ለምሳሌ እንደ የባንክ አገልግሎት(Banking service)፤ ህክምና አገልግሎት(health service)፤ ሆቴል አገልግሎት (Hotel service) እና የትራንስፖርት አገልግሎት

ዘርፍ(transportation service) የመሳሰሉት በነፃ ገበያ ውድድር ስርዓቱ መሰረት ለግል ባለሃብቱ የተፈቀዱ የአገልግሎት ዘርፎች በመሆናቸው አንድ ባለሃብት ለብቻው የንግድ ምልክት አውጥቶ ሊቆጣጠራቸው (monopolize) ሊያደርጋቸው አይችልም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮማ ቀደምቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከእኔ ሌላ ባንክ፤ ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ከእኔ ሌላ የግል ሆስፒታል፤የጣይቱ ሆቴል ከእኔ ሌላ ሆቴል፤እና ስላም ባስ ከእኔ ሌላ ሀገር አገር አቋራጭ የህዝብ ተራንስፖርት ፈቃድና እውቅና ሊሰጥ አይገባም ብለው ክስ ማቅረብ ነበረባቸው እንደማለት ነው። በተመሳሳይ ከሳሽ ራይድ(Ride) የሚለውን የወል የትራንፖርት አገልግሎት መጠሪያ የንግድ ምልክት አድርጎ ያስመዘገበበት መንገድ በራሱ ህገ ወጥ በመሆኑ የራሱን መለያ ሰረገላ ራይድ (Seregela Ride) ብሎ የንግድ ምልክት ባስመዘገበው ተከሳሽ ላይ የትኛውንም የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊያቀርብ የማይችል በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል።

ከሳሽ ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ራይድ (Ride) በሚለው የንግድ ምልክት የተፈቀደለት በሶፍት ዌር ልማት ዲዛይንና ትግበራ ስራዎች በአለም አቀፍ ምድብ 42 ስር እንጂ በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ማለትም በአለም አቀፍ ምድብ 39 ስር ፈቃድም ሆነ እውቅና አላገኘም። ስለሆነም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በአለም አቀፍ ምድብ 39 እና 42 ስር በተመዘገበው በተከሳሽ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ ስለማይችል ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ሊያደርገው ይገባል።

በንግድ ምልክት ምዘገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀፅ 7 እንዲሁም በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀፅ 16 (1,ሀ) መሰረት በሶስተኛ ወገን መብት ምክንያት መመዘገብ የማይችለው የንግድ ምልክትና የንግድ ስም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ምልክትና ስም ጋር አንድ አይነት ከሆነ ወይም ተገልጋይን ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ብቻ እንደሆነ በግልፅ ተደንግጓል። በተያዘው ጉዳይ የተከሳሽ የንግድ ምልክት ከከሳሽ የንግድ ምልክት ጋር ፊፅሞ አንድ አይነት ባለመሆኑ ማናቸውንም ተገልጋይ የህብረተሰብ ክፍል ሊያሳስት አይችልም። የከሳሽ የንግድ ምልክት በግማሽ ሰርክል ላይ "ራይድ RIDE" የሚል የአማርኛና የእንገሊዘኛ ፊድል ፅሁፍና ከጎኑ SMS 8202 የሚል ሎጎ ያለው ሲሆን በአንፃሩ ለተከሳሽ የተሰጠው የንግድ ምልክት ደግሞ በሙሉ ክብ መስመር ውስጥ ሁለት የተሸከርካሪ ጎማ ምልክት ያለበት በተለምዶ የሚታወቀው የሰረገላ ሎጎ ያለው እና ከክቡ ውጪ ደግሞ በእንግሊዘኛ "SEREGELA RIDE" የሚል ፅሁፍ ያለበት ከጎኑ ምንም አይነት የSMS ቁጥር

የለውም፡፡ ስለሆነም ሁለቱ የንግድ ምልክቶች በስምም ሆነ በሎጎ በእጅጉ የተለያየ መሆኑን በግልፅ መረዳት ይቻላል፡፡

ከሳሽ "RIDE" በተሰኘው የንግድ ምልክት ዝርዝር መግለጫ ላይ የተመዘገበለት በሶፍት ዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ ስራዎች በአለም አቀፍ ምድብ 42 ስር እንጂ በምድብ 39 ስር በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰጠው የንግድ ምልክት የለም፡፡ በአንፃሩ ተከሳሽ "SEREGELA RIDE" በሚለው የንግድ ምልክቱ የተመዘገበው በቴክኖሎጂ የታገዘ የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ በአለም አቀፍ ምድብ 39 እና 42 ስር ነው፡፡ ስለሆነም የከሳሽ የንግድ ምልክት ምዘገባና ፈቃድለሶፍት ዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ ብቻ እንጂ በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ለመስራት ባለመሆኑ የተከሳሽ ከከሳሽ የንግድ ምልክት ፍፁም የተለየ መሆኑን፤ ይልቁንም ከሳሽ ካስመዘገበውና እውቅና ካገኘበት የንግድ ምልክት የስራ ዘርፍ ውጪ ያላግባብ በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ነው፡፡

ከሳሽ የሚጠቀመው ኮድ 03 ተሽከርካሪ ያላቸውን የግል ባለሀብቶች የእጅ ስልክ ላይ የሞባይል አፕሊኬሽን በመጫን እና ትራንስፖርት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ደግሞ በአጭር የስልክ ማእከል ጥሪ 8294 ላይ በመደወል ወይም Ride Passenger et. የሚል አፕሊኬሽን በመጠቀም የግል አሽከርካሪዎንና ተገልጋዩን በማገናኘት ከሚገኘው ገቢ የኮሚሽን ስራ የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡ በአንፃሩ ተከሳሽ ወደ 150 የሚጠጉ የራሱን ተሽከርካሪዎችና የራሱን ሴት ሹፌሮች ቀጥሮ ተገልጋዩ ህብረተሰብ በአጭር የስልክ ጥሪ ማእከል 7878 ላይ እየደወለ ወይም seregela Ride የሚል አፕኬሽን በመጠቀም ከሹፌሮቹ ጋር የሚገናኝበትና አገልግሎቱን የሚያገኝበት ቀጥተኛ የሆነ የታክሲ ትራንስፖርት ሰርቪስ የሚሰጥ ድርጅት ነው፡፡ ስለሆነም ከከሳሽ የንግድ ምልክት እና አሰራር ጋር የሚመሳሰልበት መንገድ ስለሌለ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ በነፃ ውድድር ላይ የተመሰረተ አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎት ይዞ ከመምጣት ውጪ ደንበኞችን የሚያሳስትበትም ሆነ የከሳሽን ጥቅም የሚጎዳበት አንዳችም ተጨባጭ ሁኔታ የለም፡፡ በዚህ ረገድ ከሳሽ ሰረገላ ራይድ በሚለው ህጋዊ የንግድ ምልክቱን ተጠቅሜ የምሰጠውን አገልግሎት በመገናኛ ብዙሀንና በሌላ የሶሻል ሚዲያ ፕላት ፎርም እንዳላስተዋውቅ ክልከላ ለማድረግ በማሰብ ያላግባብ የቀረበውን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ እንዲደረግ፡፡

ከሳሽ ያቀረበውን ክስ የስረ ነገር ስልጣኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለማስመሰል ያህክል በድፍኑ ብር 100,000 ጉዳት ደርሶብኛል ሲል በክሱ ላይ ከመግለፅ ባሻገር በየትኛው የተከሳሽ ድርጊት ይህንን ያህክል ጉዳት እንደደረሰበት፤ የደረሰው የጉዳት መጠንስ እንዴት

ተሰልቶ ብር መቶ ሺህ እንደመጣ እንኳን በተቸባጭ ባላሳየበት፤ በተለይ ተከሳሽ ገና የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበው በሃምሌ ወር 2012 ዓ.ም በመሆኑና በመገናኛ ብዙሃንም ማስተዋወቅ የጀመረው ነሃሴ ወር መጨረሻ ላይ ሆኖ ወዲያው መስከረም ወር 2012ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ገና ወደ ስራ ሳይገባና ሳይጀምር ከሳሽ በፍ/ቤት ትእዛዝ ያሳገደው መሆኑን እያወቀ ጉዳት ደርሶብኛል ሲል ያቀረበው ክስ ሙሉ ለሙሉ ተገቢ ያልሆነ እንዲሁም የምክንያትና ውጤት ግንኙነት የሌለው (without causation or cause effect relationship) ብቻ ሳይሆን በአንዳችም አግባብነት ባለው ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል፡፡

የከሳሽ ደንበኞች የሆኑትን የታክሲና የኮድ 03 መኪና ባለሃብቶችን በሚቆሙበት ቦታ ድረስ በመሄድ ከከሳሽ ጋር ያላቸውን ውል በማቋረጥ ከተከሳሽ ጋር ቢሰሩ ተከሳሽ የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንደሚሰጣቸውና የሚያስከፍላቸውም ከከሳሽ ያነሰ ኮሚሽን እንደሆነ በመግለፅ ደንበኞቼን እያስከዳብኝ ነው ሲል ያቀረበውን ክስ ሙሉ ለሙሉ ከእውነት የራቀ ሀሰት ነው፡፡ ተከሳሽ ልክ እንደ ከሳሽ የኮድ 03 ተሽከርካሪ ያላቸውን ባለሃብቶችን ተጠቅሞ የኮሚሽን ስራ የሚሰራ ሳይሆን በስሙ የተመዘገቡትን ከ150 በላይ የሚሆኑ የራሱን የቤት አውቶሞቢሎች ራሱው በሚቀጥራቸው ሴት ሹፌሮች ለህብረተሰቡ አማራጭ የታክሲ ትራንስፖርት አግልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረበው ወቀሳና ክስ ፈፅም ምክንያታዊ ያልሆነና ምናልባትም ተከሳሽ የሚሰጠውን የታክሲ ትራስፖርት ባህሪ ወይም አሰራር ካለመረዳት የመነጨ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡በማስረጃነትም የሰነድ እና የምስክሮች ስም ዝርዝር አያይዘው አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም

1. ከሳሽ ራይድ የንግድ ምልክት አድርጎ ማስመዝገቡ የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉ የወል መጠሪያ በመሆኑ የንግድ ምልክት ጥበቃ ጥሰት በሚል ክስ ለማቅረብ ይችላል ወይስ አይችልም፣ ተከሳሽ ሰረገላ ራይድ በሚል የንግድ ምልክቱን አስመዝግቧል ወይስ አላስመዘገበም፣
2. የከሳሽ የንግድ ምልክትና ስም ራይድ የሚለውና የተከሳሽ የንግድ ምልክት እና ስም አድርጎ የሚጠቀመው ሰረገላ ራይድ አንድ ዓይነት ወይም አገልግሎቱን ለሚጠቀም ማህበረሰብ ተመሳሳይ በመሆናቸው ሊያሳስት አልያም ሊያሳክር የሚችሉ ናቸው ወይስ አይደሉም፣ ተከሳሽ ሰረገላ ከሚለው የንግድ ምልክቱ ቀጥሎ ራይድ የሚል የከሳሽ

የንግድ ምልክት እና የንግድ ስም በመጠቀሙ ጥበቃ የተሰጠው የንግድ ምልክት ጥሰት ፈፅሟል ሊባል ይችላል ወይስ አይችልም፣

3. ተከሳሽ በከሳሽ ላይ የፈፀመው የሁከት ተግባር አለ ወይስ የለም ተከሳሽ ጥበቃ የተሰጠው የከሳሽ የንግድ ምልክት እና ስም በመጠቀሙ እንዲሁም የሁከት ተግባር በመፈፀሙ በከሳሽ ላይ ኪሳራ አድርሷል ወይስ አላደረሰም፣ ኪሳራ ከደረሰ ምን ያህል ነው የሚሉትን ጭብጦች በመመስረት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

ግራ ቀኙ መካከል ያለውን አከራካሪ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቱ ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ የግራ ቀኙን ምስክሮች አስቀርቦ የሰማ ሲሆን በከሳሽ በኩል ሦስት እና በተከሳሽ በኩል ደግሞ አራት ምስክሮች ተሰምተዋል። በከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮችም 1ኛ የከሳሽ ምስክር ከነሀሴ 15 እስከ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ሰረገላ ራይድ የሚል ትራንስፖርት ካምፓኒ ከፍታችኋል ወይ እያሉ በተደጋጋሚ የራይድ አገልግሎት ሰጪዎች ሲጠይቁን ነበር። ይጠይቁን የነበሩት የኮድ-3 አሽከርካሪ ሆነው እኛ ጋር የሚሰሩ እንዲሁም ራይድ ሊመዘገቡ የሚመጡ ናቸው። በተጨማሪ በተጠቀሰው ወር እና ጊዜ ሰረገላ ራይድ ለምን አትመዘገብም እያሉ ሴቶች በመልክ የማላውቃቸው ሲንቀሳቀሱ ነበር በማለት መስክረዋል። 2ኛ የከሳሽ ምስክር በበኩላቸው የከሳሽ የኮድ 3 አሽከርካሪዎች ኃላፊ ነኝ በማለት ከ1ኛ ምስክር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ምስክርነት ሰጥተዋል። 3ኛ የከሳሽ ምስክር የራይድ ሹፌር ነኝ፤ ብዙ አገልግሎት የሚጠቀሙ ሰዎች ሰረገላ ራይድ የሚል ቅርንጫፍ ከፍታችኋል ወይ ብለው ሲጠይቁን ነበር፤ ጊዜው ነሀሴ ወር አጋማሽ ነው። አገልግሎቱን የሚጠቀም ሁሉም ሳይሆን የተወሰነ ሰው ነው የሚጠይቀው በማለት መስክረዋል።

በተከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮችም በአንፃሩ 1ኛ የተከሳሽ ምስክር የተከሳሽ የሰው ኃይል አስተዳደር ነኝ ካሉ በኋላ ሰረገላ ራይድ የተቋቋመው ነሀሴ ወር ላይ ነው። ነሀሴ 13 ቀን 2012 ዓ.ም የንግድ ምልክት ፍቃድ አግኝተናል። ነሀሴ መጨረሻ ላይ ማስታወቂያ አወጣን፤ ብዙም ሳይቆይ ጳጉሜ ላይ ቆሟል። መስከረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም ሴት አሽከርካሪዎችን መመዝገብ ጀመርን። ሰረገላ ራይድ ከሌሎች የሚለየው ሴቶችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት ነው። የትራንስፖርት አገልግሎት በጥቅምት ወር ጀምረናል። ሰረገላ የአንድ ግለሰብ ናቸው፤ ሰራተኛ ቀጥረን ነው የምናሰራው። ሰራተኞቹ ማታ መኪና መልሰው ይሄዳሉ። የትራንስፖርት አገልግሎት የምንሰጥበት መንገድ ይለያያል። ሰረገላ ራይድ የሚል ማስታወቂያ መስከረም 01

2013 ዓ.ም አልተሰራም። ራይድ ውስጥ ሴት ሹፌሮች መኖራቸውን አላውቅም። የእኛ መኪና ሱዚኪ ናቸው። ከራይድ ጋር የሚምታታ አይደለም። ሰረገላ የጥሪ ማእከሉ 7878 ነው ብለዋል። 2ኛ የተከሳሽ ምስክር ሀምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ንግድ ፍቃድ አውጥቷል፤ ሀምሌ 13 ቀን የንግድ ምልክት አውጥቷል። ነሀሴ መጨረሻ አካባቢ ሹፌሮች ለመቅጠር ማስታወቂያ አሰርቶ ነበር፤ ማስታወቂያው ጳጉሜ ውስጥ በቴሌቪዥን ታይቶ ታገደ። ኃይብሪድ ዲዛይንስ የኮሚሽ ስራ ነው የሚሰራው። ከራይድ ጋር የሚሰሩ ሴት ሹፌሮች አጋጥመውኝ አያውቅም ብለዋል። 3ኛ የተከሳሽ ምስክርም ተመሳሳይነት ያለው ምስክነት ሰጥተዋል። 4ኛ የተከሳሽ ምስክር በበኩላቸው ሰረገላ ራይድ ታክሲ ሰርቪስስ ከእኛ ጋር ህግ ድጋፍ ፈልገው ከዚህ በፊት አማክረናቸው ነበር። የንግድ ምልክት ጥሰት አለ ለማለት የተመዘገበ መብት ሊኖር ይገባል። የሁለቱንም ወገኖች ሰርተፍኬት ስንመለከት ከሳሽ የተመዘገበው የሶፍትዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ ነው። የንግድ ምልክቱ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ነው። የትራንስፖርት አገልግሎት ኃይብሪድ ዲዛይንስ አላስመዘገበም፤ በመሆኑም ምንም አይነት መብት የላቸውም። ሰረገላ ሸማቹን የሚሳስት ምንም ተግባር አልፈጸመም፤ የየራሳቸው ሎጎ አላቸው። ህጋዊ የንግድ ስም አስፈላጊ በሆነ ቦታ መጠቀም የመብት ጥሰት የሚያስብል አይደለም። ራይድ የሚለው ቃል ጂኔሪክ ነው። በንግድ ምልክት የተካተተው ሰረገላ የሚለው እንጂ ራይድ የሚለው ቃል አልተካተተም። አሁን እየተከራከርን ያለነው ሶፍትዌር ዲዛይን ሳይሆን የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤ ስለዚህ አይጥስም በማለት መስክረዋል።

የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተ በንግድ ምልክት ምዝገባ እና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 2(12) እንደተመለከተዉ የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ሰዉ ዕቃዎች ወይም አገለግሎቶቸ ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን የንግድ ምልክቱም ቃላቶችን፤ ዲዛይኖችን፤ ፊደሎችን፤ ቁጥሮችን፤ ቀለሞችን ወይም ዕቃዎችን ወይም የመያዣቸዉን ቅርጾች ወይም የእነዚህን ቅንጅቶች ሊይዝ እንደሚችል ተመልክቷል። የንግድ ምልክትን ለመመዝገብም ስልጣን የተሰጠዉ የኢትዮጵያ አእምሮዊ ንብረት ጽ/ቤት ስለመሆኑ በአዋጁ ተመልክቷል።ይህንኑ ምዝገባ ለማከናወን የማይፈቀድበት አግባብ በአዋጁ አንቀጽ 5 ሥር ተደንግጓል። ከሳሽ ራይድ የሚለውን የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበው በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሲሆን የንግድ ምልክት ተደርጎ የተመዘገበው ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉ የወል መጠሪያ ነው በማለት ተከሳሽ የሚያቀርቡት ክርክር በባህሪው የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ተደርጎ ጥበቃ እንዲያገኝ

ሊሰጥ አይገባም ነበረ የሚል ዓይነት ክርክር ነው። መሰል ዓይነት ክርክር ደግሞ ሊቀርብ የሚገባው በመደበኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሊሆን ይገባል።በዚህ አግባብ በአዋጁ አንቀጽ 36 ስር በዝርዝር ተመልክቷል።ስለሆነም የከሳሽ የንግድ ምልክት ጥበቃ እንዲያገኝ የተሰጠው በሕጉ ከተመለከተው ውጪ በወል መጠሪያ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጉዳይ ይህ ችሎት መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ፍሬ ነገር ሆኖ አልተገኘም።

ተከሳሽ ሰረገላ ራይድ “SEREGELA RIDE” በሚል የንግድ ምልክት ምዝገባ ተደርጎለት ንግድ ምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን በመግለፅ በመልሱ ላይ ክርክር እያቀረበ ቢሆንም በማስረጃነት ባቀረበው የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ በፅሑፍ ደረጃ “SEREGELA” የሚል እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል። በዚህ ችሎት የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትም “SEREGELA RIDE” የሚል የንግድ ምልክት ምዝገባ ሂደት ባለበት እንዲቆም በሚል ሆኖ ይኸው የንግድ ምልክት ምዝገባ ሂደት ተቃውሞ ያለው ሦስተኛ ወገን ለአዕምሯዊ ጽ/ቤት እንዲያቀርብ በጋዜጣ ጥሪ የተደረገለት መሆኑ ከአቤቱታው ጋር የተያያዘው ማስረጃ ያረጋግጣል።የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሐምሌ 14 ቀን 2013 ዓ/ም በላከው ምላሽ የተከሳሽ የንግድ ምልክት “SEREGELA” የሚል ሆኖ የተመዘገበበት የሥራ ዘርፍም በአለም አቀፍ ምድብ 39 ለተዘረዘረው የትራንስፖርት አገልግሎት እና በአለም አቀፍ ምድብ 42 ለተዘረዘረው የሶፍትዌር ዲዛይን ልማት እና ትግበራ ሥራዎች መሆኑን የከሳሽ የንግድ ምልክት በአንፃሩ “RIDE” የሚል ሆኖ የተመዘገበበት የሥራ ዘርፍ በአለም አቀፍ ምድብ 42 ለተዘረዘሩት የሶፍትዌር ዲዛይን ልማት እና ትግበራ ስራዎች እንደሆነ አረጋግጦ ልኳል። ከእነዚህ ማስረጃዎች መረዳት የሚቻለው የተከሳሽ የንግድ ምልክት “SEREGELA RIDE” ሳይሆን “SEREGELA” የሚል ብቻ መሆን ነው። ስለሆነም ተከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አይደለም።

ወደ ሁለተኛ አከራካሪ የሆነ ጭብጥ በተመለከተ ከሳሽ ንግድ ምልክት ጥሰት በተከሳሽ ተፈፅሞብኛል በማለት ባቀረበው ዳኝነት ላይ ተከሳሽ በዋናነት ክርክር እያቀረበ ያለው ከሳሽ የንግድ ምልክት ጥሰት ተፈፅሞብኛል በሚለው የንግድ ምልክት በትራንስፖርት ዘርፍ ለመስራት የሚያስችል በህግ ጥበቃ የተደረገለት መብት የለም፤ ከሳሽ ራሱን ሲያስተዋውቅ የነበረው በንግድ ስሙ መሆኑን እና የንግድ ስሙም ሆነ የንግድ ምልክቱ ከከሳሽ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ የከሳሽ ደንበኞች ሊያሳስትም ሆነ የከሳሽ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስበት ሁኔታ የለም በማለት ነው።

ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረበዉ የንግድ ምልክት በምዝገባ ቁጥር LTM/4239/2011 በየካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን፤ ከሳሽም እስከ ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ ለንግድ ምልክቱ ጥበቃ የተሰጠዉ መሆኑን የቀረበዉ የንግድ ምልክት የምስክር ወረቀት ያስረዳል፡፡ ይህም የንግድ ምልክት የምስክር ወረቀት በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ 501/98 አንቀጽ 15 መሰረት የተሰጠ መሆኑን እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት ከሳሽ በማስረጃነት ላቀረበዉ የንግድ ምልክት ባለቤት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የንግድ ምልክቱ የተመዘገበለት ሰዉ የንግድ ምልክቱን ከተመዘገበበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር አያይዞ የመጠቀም ወይም ሌላ ሰዉ እንዲጠቀምበት የመፍቀድ መብት የሚኖረዉ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 26(1) ስር ተመልክቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የንግድ ምልክት ባለቤት የሆነ ሰዉ ሌሎች ሰዎች የንግድ ምልክቱን ወይም ህዝብን ሊያሳስት የሚችል ማናቸዉንም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ የንግድ ምልክቱ ከተመዘገበባቸዉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ወይም ህዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳን ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ እንዳይጠቀሙ፤ የንግድ ምልክቱን ወይንም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ ያለበቂ ምክንያቶች ጥቅሙን በሚጎዳ አኳኋን እንዳይጠቀሙ እንዲሁም ሌሎች መሰል ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ለማገድ የሚችል ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 26(2)(ሀ)(ለ)(ሐ) የሚደነግግ ሲሆን አንድ አይነት መለያ ለአንድ አይነት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ሲውል የመሳከር ሁኔታ እንዳለ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 26(3) ሥር በዝርዝር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

ከሳሽ ራይድ የሚለው የንግድ ምልክት በትራንስፖርት ዘርፍ አለም አቀፍ ምድብ 39 ጥበቃ እንዲሰጠው አለመመዝገቡ እና ተከሳሽ ሰረገላ በሚል የንግድ ምልክት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ጥበቃ ማግኘቱ ራይድ የሚለው ቃል መጠቀሙ የንግድ ምልክት ጥሰት ተፈፅምብኛል በሚል ለመጠየቅ የሚያስችል መብት አለ ወይስ የለውም፣ በተለያየ የሥራ ዘርፍ የንግድ ምልክቱ መሰጠቱ የንግድ ምልክት ጥሰት ሊፈፀም የሚችልበት ሁኔታ አለ ወይስ የለም አከራካሪ ጉዳይ በተመለከተ ከሳሽ እና ተከሳሽ የተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ እንዲሁም የንግድ ምልክት ያስመዘገቡበት አለም አቀፍ ምድብ ጋር ተያይዞ የቀረበው የተከሳሽ ክርክር የንግድ ምልክት ጥበቃ ማድረግ የተፈለገበት ዓላማ አንፃር መመልከትና ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የንግድ ምልክት አላማም ዕቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች መልካም ስም እና ዝና ለማስጠበቅና በተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም

አገልግሎቶች መካከል መሳከር (confusion) በማስወገድ የንግድ ስራ የነፃ ገበያ ስርዓትን መርህ ተከትሎ እንዲሄድና የሸማቾችን ምርጫ ለማስጠበቅም የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚያደርግ ሕግ ማውጣት ማስፈለጉን ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 መግቢያ ላይ ተመልክቷል። ይህንን ዓላማ መሰረት በማድረግ በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል ክርክር የሚደረግበት የንግድ ምልክት ጥሰት በተመለከተ በዋናነት ከሳሽ ራይድ የተሰኘ የንግድ ምልክት በአለም አቀፍ ምድብ 42 የሶፈትዌር ማበልፀግ እና ትግበራ ዘርፍ ሥር አስመዝግቦ ሰርተፍኬት የተሰጠው ሲሆን በዚሁ የንግድ ምልክት የትራንስፖርት አገልግሎት ፈላጊ የሆነ የህብረተሰብ ክፍል እና የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አሽከርካሪዎች በማገናኘት ያለማው ሶፍትዌር ተግብሮ ጥቅም ላይ እያዋለ መሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የሚቻል ነው። በተመሳሳይ መልኩ ተከሳሽ ሰረገላ የተሰኘ የንግድ ምልክት በአለም አቀፍ ምድብ 42 እና 39 የሶፍትዌር ማበልፀግ እና ትግበራ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ የንግድ ምልክት ጥበቃ ተሰጥቶት በራሱ ሶፍትዌር እና ተሽከርካሪዎች ሴት ሹፌሮችን ቀጥሮ የሚያሰራ ድርጅት መሆኑም በክርክር ሂደት ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ።ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መረዳት የሚቻለው ከሳሽ በአፅምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት ጥበቃ እንዲያገኝ ያስመዘገበው ራይድ የተሰኘው የንግድ ምልክት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያገኙ የተሸከርካሪ ባለንብረቶች ከከሳሽ ፈቃድ ተሰጥቷቸው በከሳሽ በበለፀገው ሶፍትዌር የትራንስፖርት አገልግሎት ፈላጊ አገልግሎቱ ከሚሰጡት አሽከርካሪዎች ማገናኘት እየተሰራበት ከሆነ ተከሳሽ በተሰማራበት የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት በራሱ የበለፀገው ሶፍትዌር ተጠቅሞ የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ የከሳሽ የንግድ ምልት የሚጠቀም ከሆነ በአገልግሎት ተጠቃሚውም ሆነ በማንኛውም ማህበረሰብ ላይ መሳከር ሊፈጥር የሚችል የጋራ የሆነ የተሰማሩበት የንግድ ሥራ ዘርፍ ከመኖሩም በተጨማሪ ከሳሽ ያበለፀገውን ሶፍትዌር አገልግሎት ለሚፈልግ ሰው በአዋጁ በተሰጠው መብት መሰረት እንዲጠቀም ሲፈቅድለት አገልግሎቱ ከሌላ ሰው አገልግሎት የሚለይበት የንግድ ምልክቱ ሊመሳሰልም ሆነ ሊያሳክር አይገባም።

በአዋጁ አንቀጽ 26(2) ሥር የንግድ ምልክቱ ጥበቃ መብት የተፈጠረለት ሰው በተጨማሪ የህበረተሰብ መሳሳትን የሚፈጥር ተግባር የማስወገድ ዓላማ እንዳለው ያሳያል። መሰል የሆነ መሳከር መኖሩ ማስረዳት እስከተቻለ ድረስ መሳከሩ እንዲቆም እና እንዲወገድ እንዲሁም በዚህ የተነሳ ጥሰት የፈፀመው አካል ያገኘው ጥቅም ካለ መብቱ ለተጣሰበት እንዲከፍል ዳኝነት የመጠየቅ መበት መኖሩን ከአዋጁ ድንጋጌዎች ዝርዝር ይዘት መረዳት የሚቻል ነው። ስለሆነም

ከሳሽ እና ተከሳሽ የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ መሰረት ባደረገ መልኩ የንግድ ምልክት ጥበቃ በትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ጥበቃ ለከሳሽ አልተሰጠም በማለት ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ፍርድ ቤቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

ተከሳሽ በማስታወቂያ ሲያስነግር የነበረው በንግድ ስሙ እንጂ በከሳሽ የንግድ ምልክት እና የንግድ ስም አይደለም በማለት ተከሳሽ ክርክር አቅርበዋል፡፡ከሳሽ በአንዳሩ ተከሳሽ ሰረገላ ራይድ በሚል የተሰጠው የንግድ ስም የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 2(10) እና (11) ሥር የንግድ ስም ማለት አንድ ነጋዴ ለንግድ ሥራው የሚጠቀምበት እና በህብረተሰቡ ዘንድ በግልጽ የሚታወቅበት ስም መሆኑን እንዲሁም የንግድ ድርጅት ስም ማለት ደግሞ አንድ የንግድ ድርጅት ለንግድ ምዝገባ የሚጠቀምበት፣ በመዝጋቢው መሥሪያ ቤት እና በሦስተኛ ወገኖች የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑ የሚታወቅበት ስም መሆኑን ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 15 ሥር የንግድ ድርጅት ስም በንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የሚመዘገብ ሲሆን የንግድ ስም የራሱ የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ በንግድ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ላይ የሚመዘገብ እንደሆነ በግልፅ ልዩነታቸው ያስቀምጣል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው የንግድ ስም እና የድርጅት ስም የተለያየ ዓላማ ያላቸው እንዲሁም የሚገኙበት አግባብ በራሱ መለያየቱ ነው፡፡ የተከሳሽ የድርጅት ስም “ሰረገላ ራይድ ታክሲ ሰርቪስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር” ሲሆን ተከሳሽ “ሰረገላ ራይድ” በሚል የተሰጠው የንግድ ስም መኖሩን ያቀረበው የንግድ ስም ምዝገባ ምስክር ወረቀትም ሆነ ክርክር የለም፡፡ተከሳሽ ሰረገላ ራይድ የሚል የንግድ ስም ሳይኖረው በንግድ ስሜ ነው ማስታወቂያ የሰራሁት በሚል የሚያቀርበው ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አይደለም፡፡

ተከሳሽ ካስመዘገበው የንግድ ምልክት በተጨማሪነት ሰረገላ ራይድ በሚል ማስታወቂያ መስራቱም ሆነ የሚሰጠው አገልግሎቱን ለህብረተሰብ መለያ መሆኑን ገልፃ ማቅረቡ ከከሳሽ የንግድ ምልክት ጋር መሳከሩን ይፈጥራል ወይስ አይፈጥርም የሚለው አከራካሪ ነጥብ ከህጉ አንፃር የግራ ቀኙ ማስረጃ ሲመረመር የቀረቡት የከሳሽ ምስክሮች የከሳሽ ደንበኞች ሰረገላ ራይድ የሚል ቅርንጫፍ የከፈተ መሆኑን የጠየቁ መሆኑንና ከሳሽም በዚህም ስም ቅርንጫፍ የሌለው መሆኑን መልስ የሰጠ መሆኑን ያስረዱ ሲሆን ተከሳሽ ማህበር ከሳሽ በንግድ ምልክትነት አስመዝግቦ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት መሆኑን ከከሳሽ በተለየ መልኩ ተከሳሽ ያበለፀገው ሶፍትዌር ራሱ ለሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት መተግበሩ እና ከሳሽ ደግሞ ለሌሎች ለሚሰጡት የትራንስፖርት አገልግሎት ሶፈትዌሩን

በመተግበር ጥቅም ላይ በማዋል እንደሚገለገልበት ከቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ሲሆን የከሳሽ ምስክሮችም ተከሳሽ ሰረገላ ራይድ በሚል ስያሜ እየተጠቀመ ያለ በመሆኑ የከሳሽን ሶፍትዌር በመጠቀም የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ አሽከርካሪዎች እና የትራንስፖርቱ ተጠቃሚዎች ሰዎች ዘንድ መሳከርን የፈጠረ መሆኑን ያስረዱ ሲሆን የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎችም ተከሳሽ ሰረገላ ራይድ በሚል የማስታወቂያ ስራ የሰራ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር የሚለያቸው በሚል ያቀረባቸው ምክንያቶች ከሳሽ በሌሎች ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሶፍትዌር ትግበራው ማድረጉና ተከሳሽ በራሱ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ሂደት ሶፍትዌሩን ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረጉ፣ የአሽከርካሪዎቹ በተከሳሽ በኩል ሁሉም ሴት ሹፌሮች መሆንና የሚጠቀሙት የአጭር መልዕክትም ሆነ የድምፅ ጥሪ ማድረጊያ መስመር ቁጥር መለያትን በተመለከተ በዋናነት የንግድ ምልክቱ መጠቀሙን ህብረተሰቡን ሊያሳክር ወይም ሊያሳስት የሚችል የንግድ ምልክት አለመሆኑን ለማስረዳት ቢሆንም በከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በአንፃሩ የከሳሽ የንግድ ምልክት ሆነው ራይድ የተሰኘ ቃል ከተከሳሽ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ላይ በተከሳሽ ሰረገላ ራይድ በሚል ማስታወቂያ ተሰርቶ ተከሳሽ የሚሰጠው አገልግሎት ለማስተዋወቅ አገልግሎት መስጠቱ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የከሳሽ ደንበኖችን እና የትራንስፖርት አገልግሎት በከሳሾች ሶፍትዌር አማካኝነት የሚያገኙ ግለሰቦች መሳከራቸውን ተከትሎለድርጅቱም ሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ አሽከርካሪዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ እንደነበረ አስረድተዋል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ በህጉ ካስመዘገበውና ጥበቃ ከተደረገለት “SEREGELA” የተሰኘ ንግድ ምልክት በተጨማሪ የከሳሽ የንግድ ምልክት አካቶ “SEREGELA RIDE” በሚል የሚሰጠው አገልግሎት ማስተዋወቁም ሆነ አገልግሎቱን ለመስጠት የንግድ ምልክቱ አካቶ መጠቀም እንደሚችል የሚቀርበው ክርክር የከሳሽን ጥበቃ የተሰጠው መብት የሚጥስ ተግባር በመሆኑ ራይድ (RIDE) የሚለውን ቃል በመጠቀምም በማንኛውም የመገናኛ ብዙሀንም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያዎች የማስታወቂያ ስራዎችን እንዳይሰራ በማለት ፍርድ ቤቱ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ሦስተኛው ጭብጥ በተመለከተ ተከሳሽ በከሳሽ ላይ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ በማለት ከሳሽ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ተከሳሽ በአንፃሩ ክደው ተከራክረዋል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1149 (1) ላይ እንደተመለከተው ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሳበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንደሚመለስለት ወይም የተነሳው ሁከት እንዲወገድለት እንዲሁም

ስለደረሰበት ጉዳት ኪሳራ ለመጠየቅ የሚችል መሆኑ የተመለከተ ሲሆን ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1140 የህግ ድንጋጌ ለመገንዘብ እንደሚቻለውም ሁከት ተፈጥሮብኛል በሚል ክስ የሚያቀርብ ሰው በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ይዞታውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመገልገል መብቱ የተጣሰ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በተከሳሽ የተፈፀመ የሁከት ተግባር ስለመኖሩ ከሳሽ ያቀረቡት ማስረጃ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ ከሳሽ ያቀረበው ዳኝነት በማስረጃ ባለመደገፉ ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተከሳሽ የከሳሽ የንግድ ምልክት ጥሰት በመፈፀሙ እና የሁከት ተግባር በመፈፀሙ ያደረሰው ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ተከሳሽ በአንዳኑ የንግድ ምልክቱ አስመዝግቦ ወደ ሥራ ሳይገባ በፍርድ ቤት የታገደ እና የጉዳት ካሳ መጠኑ በምን አግባብ ብር 100,000 እንደሚሆን በክሱ ስላልተገለጸ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡

በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 40 ሥር የንግድ ምልክት መብት መጣስን አስመልክቶ የቀረበለት ፍርድ ቤት የመብቱ መጣስ ከማስቆም በተጨማሪ የካሳ ክፍያ ሊወስን እንደሚገባ እና የካሳ መጠኑንም መብቱ የጣሰው በንግድ ምልክቱ በመጠቀም ካገኘው ገቢ ላይ የተጣራ ትርፍ እና በንግድ ምልክቱ የመጠቀም መብት የሚፈቀድለት ቢሆን ኖሮ ይጠየቅ የነበረው የሮያሊቲ ክፍያ መካከል የሚበልጠውን ሊወሰን እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው የንግድ ምልክቱን ጥሰት ፈፅሞ ያገኘው ጥቅም ያላግባብ መበልፀግ ስለሆነ መብቱ ለተጣሰበት የንግድ ምልክቱ ባለቤት ሊከፍል እንደሚገባ ሲሆን ከዚህ አንፃር ተከሳሽ የንግድ ምልክቱን የተወሰኑት ቀናት በቴሌቪዥንና በበማህበራዊ ሚዲያ ማስታወቂ ከመስራቱ ውጪ ወደ ሥራ ገብቶ በንግድ ምልክቱ የተጠቀመ አለመሆኑ በተከሳሽ በኩል ከቀረቡት ምስክሮች ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል፡፡የካሳ ክፍያው ጉዳት በመኖሩ ምክንያት ተመዛዛኝ ካሳ እንዲከፈል የሚል ሳይሆን በመብቱ መጣስ የተገኘ ጥቅም ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ መሆኑ ሲታይ በከሳሽ በቀረበው ክርክር አግባብ የካሳው መጠን በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2102 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በርትዕ ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡ስለሆነም ተከሳሽ የንግድ ምልክት ጥሰት በፈፀመበት ወቅት የንግድ ምልክቱ ተጠቅሞ ያገኘው ጥቅም መኖሩ ማረጋገጥ ባለመቻሉ ተከሳሽ ብር 100,000 የጉዳት ካሳ እንዲከፍል በከሳሽ የቀረበው ዳንነት ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. ተከሳሽ በንግድ ምልክትንት ካስመዘገበው “SEREGELA” ከሚለው ቃል በተጨማሪነት ከሳሽ በንግድ ምልክትነት ያስመዘገበውን ራይድ (RIDE) የሚለውን ቃል በንግድ ስሙም ሆነ በንግድ ምልክቱ ማካተቱም ሆነ በዚህ አግባብም ማስታወቂያ ማስነገሩ ከሳሽ በንግድ ምልክትነት ያስመዘገበውን ጥበቃ የተደረገለትን መብት የሚጥስ ሕገ ወጥ ተግባር በመሆኑ ተከሳሽ ራይድ (RIDE) የሚለውን ቃል ከንግድ ስሙም ሆነ ከንግድ ምልክቱ እንዲያወጣ እንዲሁም ራይድ (RIDE) የሚለውን ቃል በመጠቀምም በማንኛውም የመገናኛ ብዙሀንም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያዎች የማስታወቂያ ስራዎችን እንዳይሰራ በማለት ተወስኗል፡፡
2. ከሳሽ በተከሳሽ የተፈጠረ የሁከት ተግባር እንዲወገድ በማለት ያቀረበው ዳኝነት በማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡
3. ተከሳሽ በፈጸመው የንግድ ምልክት ጥሰት ምክንያት ያገኘው ጥቅም መኖሩ ስላልተረጋገጠ እንዲሁም የተፈፀመ የሁከት ተግባር ባለመኖሩ የጉዳት ካሳ ተከሳሽ እንዲከፍል በከሳሽ የቀረበው ዳኝነት ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡
4. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት የወጣ ወጪና ደረሰ ኪሳራ የሚያሳይ ዝርዝር ከሳሽ በተከሳሽ ላይ የማቅረብ መብት ተጠብቋል፡፡

ትዕዛዝ

- በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚፈልግ ወገን የመዝገቡ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዲላክ ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለበት፡፡